# <u>የኢሕአፓና ትርምስ ዑደትና የኢትዮጵያ ሠራተኞች</u>

<u>ከዳዊ ኢብራሂም</u>

ማንም ወደ ሕሊናው ተመልሶ ማሰብ የሚችል ሁሉ እንደሚገነዘበው፣ ባለፉት ሰላሣ ዓመታት በሀገራችን የታየውን ትርምስ አንስቶ ኢሕአፓን መርሳት፤ ኢሕአፓን አንስቶ ትርምሱን ችላ ማለት የሚቻል አይመስለኝም። ይኸ የኢሕአፓ-ትርምስ፣ የትርምስ-ኢሕአፓ ጥምረት ባለፉት ሁለት ወራት በአዲስና በስፋት የተያዘ ይመስላል። ትርምሱ በስፋት በመቀነባበር ላይ ለመሆኑም፣ የተለያዩ ምልክቶች እየታዩ ናቸው። ከነዚህም ውስጥ፣ በቅንጅት ካምፕ ላይ በመካሄድ ላይ ያለውን በተለያዩ ድኅረ-ገጾች ያነበብን ሲሆን፤ በኢትዮጵያ ሠራተኞችም ስም፣ ከአለፈው ዓለም አቀፍ የሠራተኞች ቀን (May-day) ጀምሮ፣ በጥቂት (ከአምስት በማይበልጡ) ፈርጣጭ የማኅበራት መሪዎች አማካይነት የኢሕአፓ ተለጣፊ ኢሚገሬ ድርጅታዊ መረብ ለመጣል ከንቱ ሙከራ እየተደረገ ነው።

ምንም እንኳን በአስገዳጅ ሁኔታ ብሰደድና ከማኅበራት መዋቅር ውጭ ብሆንም፤ ባለብኝ ኃላፊነት መሠረት፣ ይኸ ዓይነት ደባ በኢትዮጵያ ሠራተኛ ማኅበራት፣ ወይም በኢትዮጵያ ሠራተኞች፣ ወይም በተሰደዱ የማኅበራት መሪዎች ስም ሲፈፀም፣ በቸልታ ማየት ስለማልችል፤ በመጠንሰስ ላይ ያለውን ደባ በተለይ የኢትዮጵያ ሠራተኞች፣ በአጠቃላይ የኢትዮጵያ ሕዝብ እንዲያውቁት ማድረጉን አስፈላጊ ሆኖ አግኝቼዋለሁ።

ኢሕአፓ ባለፈው ሚያዚያ 23፣ 1999 (May 1, 2007) ፣ የዓለም አቀፍ ሠራተኞች ቀን በዓልን አንተርሳ፣ "በአሲምባ ቡድን (Asymbba Group) አዘጋጅነት፣ የቀድሞውን የኢሠማኮ ዐቃቢ-ንዋይ፣ የአሁኑን የኢዴኃጎ ድጋፍ ኰሚቴዎች ኃላፊ፣ አቶ ደምሴ ኦሉማን የክብር ተናጋሪ አድርጋ አቀረበች። በዚያው ላይ የንግድ...ሠራተኛ ማኅበራት ፌዴሬሽን ፕሬዚዳንትና የኢሠማኰ ጠቅላይ ምክር ቤት አባል የነበረው ኃይሉ ኡርጌሣ፤ የጠቅላይ ምክር ቤት አባልና የኰንፌዴሬሽኑ የባሕር-ዳር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ጻሓፊ የነበረው ጌታቸው አበራ እና ሌሎችም ሁለት በኢሕአፓ ሰንሰለት የተያዙ ተሣታፊዎች ቀርበው 'የሜይ-ዴይ' ዲስኩር ይደረጋል። በመጨረሻም፣ በአዘጋጁ የአሲምባ ቡድን አሳሳቢነት የመነጋገሪያ ክፍሉ ቋሚ እንዲሆን ይወሰናል። በውሣኔውም መሠረት፤ "ጓዳቸው" ኃይሉ ኡርጌሣ 'የፓል-ቶክ ሩም' ከፍቶ "የላብ-አደሩ ያቸንፋል! የእንበርታ!" ወዘተ መፈክር በመፈከር ላይ ሲሆን፤ በአሁኑ ሰዓት "የኢትዮጵያ ሠራተኞች ድምፅ፣ ወይም የኢትዮጵያ ሠራተኞች ጥምረት፣ ወይም የኢትዮጵያ ሠራተኞች የዲሞክራሲና የሰላም መድረክ" የተሰኘ "ድርጅት" ለማወጅም ደንብ በመረቀቅ ላይ ነው።

ይኸ ቅንብር ድንገተኛ አይደለም። ሰፊ ጥናት የተደረገበትና ዕቅድ ወጥቶለት አመቺ ጊዜ ሲጠበቅለት የቆየ ሤራ ነው። ቅንብሩን በአይነ-ሕሊና የሚቃኙ ሁሉ፣ የቅንብሩ ሥዕል የሚሰጠውን የተሟላ ትርጉም መረዳት የሚያዳግታቸው አይደለም። ሁሉም አስቀድሞ በኢሕአፓ ድርጅታዊ ሴራ የተቋጨ ለመሆኑ፣ የታሪክ ንብረት የሆነ የአሲምባ-ቡድን አዘጋጅነትን፣ ከተናጋሪ የኢዴኃጎ ድጋፍ ኰሚቴዎች ኃላፊና ጉባኤ አስተናጋጅ ጋር፤ እነዚህን ሁለቱን ኩነቶች መልሶ ከሰንሰለት ተያዥ ተሣታፊነት ጋር አገጣጥሞ/አገናኝቶ ማየቱ በቂ ይሆናል። ሁሉም እንደሚገነዘበው፣ ሥዕሉ በኢሕአፓ መደብ (background) ላይ ከሠራተኛ ማኅበር እምነት ባፈተነገጡ ግለሰቦች ገጽታ (profile) የተሠራ ሥዕል ነው። ሥዕሉ በኢሕአፓ ማዕቀፍና ልክ ላይ የተቀረፀ የሠራተኞች ቀን "የአዞ እምባ አምቢ ምስሎች" ተብሎም ሊወሰድ ይችላል። ከዚህም ባሻገር፣ ግለሰቦቹ የቆሙበትን ሥፍራና ከማን ጋር እንደሚያዘጠዝጡ የሚያውቁ፤ ግለሰቦቹ በሚኖሩበት አካባቢ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ደግሞ ከሥዕሉ ግጥምጥም ትርጉም በተጨማሪ እየተሠራ ያለው ድራማ የማን እንደሆነ በይበልጥ፣ ግፍ ለበረከተባቸው የኢትዮጵያ ሠራተኞች ለእውነት ሲሉ እንደሚገልጹ ተስፋ አደርጋለሁ።

ከዚሁ ከጥረቱ ገጽታ ጋር ተያይዘው የሚነሱት የትርምሱ እንድምታዎች ምንድርናቸው የሚሉ ጥያቄዎች ናቸው። አንዱ እንድምታ የሥረዓተ-አልበኝነት (anarchism) ዝንባሌ በሠራተኛው እንቅስቅስቃሴ ውስጥ ዳግም እንዲያቆጠቍጥ ሩጫ መጀመሩ ነው። ሁለተኛው በዚሁ ቡድን በ1960ዎቹ ሁለተኛ አጋማሽ በኢትዮጵያ ሠራተኞች ላይ የወረደውን ግፍ፤ የታየውን ምስቅልቅልና የተፈጠረውን ትርምስ ከታሪካችን ለቅመን እንድናስታውስ የሚገፋፋ ነው። ሦስተኛው አንድ አዋኪ ግለሰብ በኢሠማኮ ውስጥ አሰርጐ ከማስገባት አንስቶ፣ ለስደት ከተዳረግንም በኋላ የተከፈቱብን መጠነ-ሰፊ ዘመቻዎችና የተፈጠሩብን አያሌ መሰናክሎች፣ ከ60ዎቹ ምስቅልቅሎች ጋር ያላቸውን ተዛመጅነት የሚያመላክት ሲሆን፤ አራተኛው እንድምታ፣ ስንዝር መንፏቀቅ ባይችል እንኳ፣ ሊያስከትል የሚችለው ግራ የማጋባት ውጤት ነው።

የሥረዓተ-አልበኝነት (anarchism) ዝንባሌ በሠራተኛው እንቅስቃሴ ውስጥ ዳግም እንዲያቆጠቁጥ የተፈለገው፣ አናርኪዝም በበሕርዩ የብዙሃን ንቅናቄ (mass movement) አነፍናፊ ከመሆኑ የመነጨ፣ ነው። አያሌ በሥረዓተ-አልበኝነት ላይ የተጻፉ ሥነ-ጽሑፎች እንደሚያመለክቱት፣ ሥረዓተ-አልበኞች የተገፉ፣ መብትና ነፃነት የተቀሙ የሕብረተሰብ ክፍሎችን፤ በይበልጥም ደግሞ፣ የኢንዱስትሪ ሠራተኞችን በሥርዓት-የለሽ አብዮታዊ ማኅበራተኛነት (anarcho-syndicalism) በማደራጀት ሕዝባዊ ገጽታ ለመላበስ እንደሞከሩ ታሪክ ይመሰክራል። በተመሳሳይ ሁኔታም፣ ከላይ በተመለከተው ድርጊቷ፣ ኢሕአፓ በአሁኑ ጊዜ በሀገራችን ያለውን

የሠራተኛ መብት መታጣት፣ የነፃነት ገፋፋና የድምፅ አፈና ለራሷ ጠቀሜታ ለማዋልና ሙሉ በሙሉ ከተነጠለችበት ሕዝባዊ እንቅስቃሴ ጋር ለመተሣሠር፤ የብዙሃን ንቅንቄ ባለበት ሁሉ እያነፈነፈች ከቻለች ሕዝባዊ ገጽታ እንዲኖራት ማድረግ፣ አለያም "እኔን ካልቀናኝ ማንንም አይቅናው" በሚል ትርምስ ለመፍጠርና መሰናክል ለመሆን ከንቱ ጥረት እያደረገች ነው።

ይህም፣ በ1960ዎቹ ሁለተኛ አጋማሽ፣ ኢ.ሕአፓ በኢትዮጵያ ሠራተኞችና በማኅበሮቻቸው ላይ ያወረደችውን ግፍ እንደገና ለመድገም ሽር-ጉድ እያለች መሆኑን ያመላክተናል። ከ1967 እስከ 1969 ዓ.ም ድረስ ኢ.ሕአፓ በኢትዮጵያ ሠራተኞችና በማኅበሮቻቸው ላይ ያደረሰችው ጉዳት ይቅር የማይባል ዘግናኝና አሳዛኝ እንደ ነበረ፤ በሠራተኛ ማኅበሩ ውስጥ ከሚገኙ ማኅደሮች፣ ከሕያው ምሥክሮችና ከሌሎችም የጽሑፍ ማስረጃዎች መረዳት ይቻላል። ለዚሁም ሠራተኛን የሚመለከቱ የክፍሉ ታደሰንና የአንዳርጋቸው አሰግድን መጽሓፍት አንዳንድ ርዕሶች መመልከት ይቻላል።

ከነዚሁ የታሪካችን ምንጮች መገንዘብ እንደሚቻለው፣ ኢ.ሕአፓ (ኢ.ሕአድ ትባል እንደነበረች) በ1966፣ በኢትዮጵያ ሠራተኞች አንድነት ማኅበር (ኢ.ሠአማ)- ውስጥ ሠርጋ በመግባት፤ አቶ ክፍሉ ታደስንና ሥዩም ከበደን በማኅበሩ ውስጥ በሠራተኝነት አስቀጠረች። ሁለቱም የማኅበሩ 'የሠራተኛ ድምፅ' ጋዜጣ አዘጋጅ እንዲሆኑ አደረገች። በሂደትም ጋዜጠውን ከተመሠረተበት ዓላማ ውጭ በማውጣት- "ለኳሽና ተንኳሽ" ጽሑፎች ወደሚወጡበት የቡድኑ ልሣን ቀየረች (አንዳርጋቸው፡ ገጽ፡ 178)። የሠራተኛውን ልሣን ለራሷ የፖለቲካ መሣሪያ ከመድረጓም ባሻገር፣ ሥዩም ከበደ የኢ.ሕአፓ "የከተማ ትጥቅ ትግል"-(እነርሱ እነደሚሉት "የጥቃት መከላከል") ዋና መሪ ስለነበረ፣ የሠራተኛውን ብሔራዊ ጽ/ቤት የግድያ ዕቅድ ማውጫ፣ የቦምብ አንጋቢ ሽብርተኞች (bomb-totting-terrorists) መወናጨፊያና የመቺ ቡድን (death squad) መጠለያና መሸሸጊያ አደረገች። የማኅበሩ ሕንፃ ከመሬት በታች፤ ምድር ቤት የተገነባለት በመሆኑም፣ ለምሥጢራዊ የጦር መሣሪያዎች መደበቂያ ምቹ ሥፍራ አድረጋ ቆየች። የዚህ ዓይነቱን ድርጊት በሠራተኛ ማኅበር ግቢ ውስጥ ማካሄድና ሠርጐ-ገብነት በዓለም አቀፍ የመደራጀት ነፃነት ድንጋጌዎች (conventions) መሠረት ፍጹም የተከላከለ ነው። የሠራተኛ ማኅበሩን ለዚህ ዓይነት ሕገ-ወጥ ተግባር መጠቀሙ ቀርቶ፣ ግቢውን መርገጡ ራሱ ዓለም አቀፍ የድርጅታዊ ነፃነት መርሆዎችን የተጋፋ ግልጽ ውንብድና ነበር።

እነ ኃይሉ ዑርጌሣ የሚሠሩት ለዚህ ቡድን ነው። የተደራጁት ከነዚህ ጋር ነው። የሜይ-ዴይን መታሰቢያ በዓል የሚያስታውሳቸውና የሚያዘጋጅላቸው ይኸ ቡድን ነው። በዓሉን የሚያከብሩት፣ የሠራተኞችን የመብት ጥያቄዎች የሚያነሱት፣ ይህን ዓይነት የሠራተኛ ልሣን ከቀማ፣ የማኅበር ግቢ (premises) ከተዳፈረና ማኅበሩን ለወንጀል ተግባር ካዋለ ቡድን ጋር ነው።

ኢ.ሕአፓ የሠራተኛውን ጋዜጣ በመቆጣጣሩና የማኅበሩን ጽ/ቤት የነፍስ ገዳዮች ዋሻ በማድረጉም ብቻ አልተወሰነችም። በወቅቱ የፖሊት ቢሮ አባሏ የነበረውን አቶ ግርማቸው ለማ በኢ.ሠአማ የትምህርትና ሕዝብ ግንኙነት ክፍል ውስጥ በሽፋን እንዲሠራ አድርጋ፤ እርሱና አቶ ክፍሉ የሚመሩት የራሷን "የሠራተኛ ኰሚቴ" አቋቁማ፣ ከማኅበሩ ጽ/ቤት እሰከ ኢኰኖሚ ተቋማት ድረስ ሠራተኞችን መመልመሉን ተያያዘች። የመለመለቻቸውን ሠራተኞች፣ በጥናት ክበቦችና፣ በሕዋሶች ይዛ፣ በሕቡዕ በማሰባሰብ ማኅበሩን የምትቆጣጠርበት ሥልት ነደፈች። ምልምሎቿንም "ተራማጅ የሠራተኛ ማኅበር መሪዎች" የሚል ስያሜ ሰጥታቸው የኢ.ሠአማ ተቃዋሚ አንጃ ፈጠረች። በነዚህ መሣሪያነትም በወቅቱ የኢ.ሠአማ ፕሬዝዳንት የነበሩት አቶ በየነ ሰለሞን ከሶስት ባልደረቦቻቸው ጋር የመታሠራቸውን፣ አጋጣሚ ተጠቅማና፣ ሳይታሠሩ የቀሩትን መሪዎች ባደራጀችው አንጃ ወጥራ ማኅበሩን ሙሉ በሙሉ ለመቆጣጠር ትግሏን አፋፋመች። ኢ.ሠአማ ከውጭ በሁለት አማቂ ኃይሎች፣ በውስጥ ደግሞ በግጭትና በክፍፍል ተወጥሮ፣ ችግሩ እንዲወሳሰብ ተደረገ። መሠረታዊ ችግሩም ኢ.ሕአፓ በአንድ በኩል፣ ደርግ በሌላ በኩል ማኅበሩን ከበው በየፊናቸው በቁጥጥራቸው ሥር ለማዋል ያደርጉት የነበረው ጦርነት ነበር። በዚህም የማኅበሩ ጽ/ቤት፣ የምርት ወለሎችና የአገልግሎት መስጫ መስኰች የፍልሚያ ሜዳ ሆኑ። በፍልሚያው አቶ ዓለም አብዲ በደርግ ጐራ፣ አቶ ማርቆስ ሐጐስ በኢ.ሕአፓ ጐራ ተሰለፉ። ኢ.ሕአፓ የጥፋት ዘመቻዋን ግንባር በማስፋት ፍልሚያዋን ወደ አዲስ አበባና አከባበቢው የኢ.ሠአማ ቅርንጫፍ ማኅበር አስፋፋች። ከአዲስ አበባና አካባቢው፣ የተመለመሉትን ጭፍሮቿን ሰብስባ፣ የቅርንጫፍ ማኅበሩን መሪ አቶ ጣዕምያለው እሼቴን በሌሉበት እንዲገለብጡ አደረገች። አቶ ጣዕምያለው ለሕገ-ወጥ ግልበጣው እወቅና ለመስጠት ፈቃኛ ባለመሆናቸውና ብሔራዊ ማኅበሩን ከኢ.ሕአፓ አንጃኞች በመከላከላቸው፤ ኢ.ሕአፓ በአቶ ጣዕምያለው እሼቴ ላይ ከስድሰት ጊዜ ያለነሰ የመግደል ሙከራ አደረገችባቸው። ቅርንጫፍ ማኅበሩም እንደ ብሔራዊ ማኅበሩ ታመሠ።

ቀጥላም፣ ኢ.ሕአፓ የኢ.ሠአማን ጽ/ቤት በመቆጣጠር በማኅበሩ ላይ መፈንቅለ-ማኅበር አካሄደች። አቶ ማርቆስ ሓጐስ የኢ.ሠአማ ፕሬዚዳንት መሆኑን ኢ.ሕአፓ በገሃድ ስታውጅ፣ በማኅበሩ ውስጥ የፈጠረችው አንጃ በበኩሉ፡ የኢ.ሠአማ ጊዜያዊ አስተባባሪ ኮሚቴ እንደመሠረተ አስታወቀ። በዚያው "ጊዜ ጊዜያዊ አስተባባሪ ኰሚቴው" የኢ.ሠአማን ጠቅላይ ምክር ቤት በገዛ ፈቃዱ አፈረሰ። የፓርቲ ፖሊቲካ የሠራተኛ ማኅበር እንቅስቃሴን ተካ። ይህ ሁሉ ሲፈፀም ኢ.ሠአማ በሶስት ቅርንጫፍ ማኅበራት የተደራጀ ማኅበር ስለነበረ፣ በአዲስ አበባና አካባቢው ሠራተኞች ብቻ ሊወከል የማይችል መሆኑ በይፋ እየታወቀ ሆነ ተብሎ ተጣሰ። ድርጊቱ የአካባቢው ማኅበራት እንኳን ተወያይተውበትና አምነውበት በወከሏቸው ተወካዮች አማካይነት የተላለፈ ውሣኔም ባለመሆኑ ተራ

ማጭበርበር ነበር። አካሄዱም በማኅበሩ ደንቦች መሠረት የተፈፀመ ባለመሆኑ የለየለት ሥርዓት-የለሽ (lawlessness) አፈፃፀም ነበር። በአጭሩ፣ ኢሕአፓ የኢሠአማን የውስጥ አሠራሮችና ደንቦች በአፍጢማቸው ደፍታ ማኅበሩን አተረማመሰች። ደርግም እነዚህን ቀዳዳዎች ተጠቅሞ፣ ምክትል ፕሬዚዳንቱ የኢሠአማ ሕጋዊ ተጠሪ መሆናቸውን ገለፀ። ኢሕአፓ በዚህም ሳትገታ፣ ትንቅንቁን ቀጥላ፣ የማኅበሩን ጽ/ቤት ባደራጀችው አንጃ በግርግር ስትይዝ፣ የበለጠ ጉልበት ያለው ሲያስለቅቃት፣ መልሳ ስትይዝና እንደገና ስትባረር፣ የማኅበሩ ጽ/ቤት እንዲዘጋ አደረገች።

እነ ኃይሉ ዑርጌሣ የሠሩትና እየሠሩ ያሉት ለዚህ ቡድን ነው። የተደራጁት ከነዚህ ጋር ነው። የሠራተኞች የመደራጀት መብትና ድርጅታዊ ነፃነት በዕለተ ሜይ-ዴይ የሚዘክሩት ይህን ዓይነት የሠራተኛ ማኅበራት ነፃነት ከተዳፈረና የሠራተኛ ማኅበራት መንፈስ (trade unionism spirit) እስከወዲህም ድረስ እንዲደበዝዝ ከፍተኛ ወንጀል ከፈፀመው ቡድን ጋር ነው።

ኋለም፣ ኢሕአፓ የማኅበሩን መዘጋት እንደ መቀስቀሻና ማነሳሻ መሣሪያ ተጠቅማበት በትርምሷ ገፋችበት። የጥናት ቡድኖቿን በፈጠረችው የኢሠአማ ተቃዋሚ አንጃ ዙሪያ በማሰባሰብ የሥራ ማቆም አድማ ኰሚቴዎች ፈጥራ ሥራ ለማስቆም ተንቀሳቀሰች። በነዚህም ከአንዴም ሁለቴ “የሥራ ማቆም አድማ” ጠርታ ሳይሳካላት ቀረ። በተለይም መስከረም 12/1969 ከጠራችው ሥራ ማቆም ጋር ኰሎኔል መንግሥቱን የመግደል ሙከራ ስላጣመረች፣ ሠራተኛው እንዲሸከመው የተጫነበት ዕዳ፣ እንዲከፍለው የተፈረደበት የደም ዋጋና እንዲቀበለው የተደረገው ሠቆቃ እጅግ ከባድ ነበር። በምላሹም፣ ደርግ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ አውጥቶ፣ በኢትዮጵያ ሠራተኞች ላይ ታይቶ የማይታወቅ ግፍ ወረደ። በርካታ የሠራተኛ ማኅበራት መሪዎች ታሠሩ። ከፊሎቹ ከማኅበር መሪነት ተባረሩ። በብዙ መቶዎች የሚቆጠሩ ሠራተኞ ታፈሱ። በአቃቂ በርካታ ሠራተኞች ተረሸኑ። በአየር መንገድ 13 ሠራተኞች ሞቱ፣ ከሰላሣ የማያንሱ ቆሰሉ። ለኢሕአፓ የሥልጣን መወጣጫ፣ ሻካራ የምርት እጆችን አፈር በላቸው። ኢሠአማም ከነአካቴው ተዘጋ።

እነ አቶ ኃይሉ ዑርጌሣ የሚሠሩት ለዚህ ቡድን ነው። የሚደራጁት ከነዚህ ጋር ነው። የሜይ-ዴይን መታሰቢያ በዓል የሚያስታውሳቸውና የሚያዘጋጅላችው ይኸ ቡድን ነው። በዓሉን የሚያከብሩትና፣ የሠራተኞችን መስዋዕትነት የሚዘክሩት፣ ይህን ዓይነት የሠራተኛ በሕይወት የመኖር ሰብአዊ መብት ከጣሰ፣ የሠራተኛ ደም እንዲጐርፍ ካደረገና ከማኅበራት መሠረታዊ መብቶች አንዱ የሆነው “ሥራ የማቆም መብት” (the right to strike) እስከዛሬም ድረስ ትርጉም እንዲያጣ ካደረገ ቡድን ጋር ነው።

ኢሕአፓ በዚህ ዓይነት ሠራተኛው እንዲደማና ግፍ እንዲወርድበት እያደረገች ትንቅንቋን የሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁ 64/68 እስከወጣበት ጊዜ ቀጠለች። አዋጁን “የባርነት አዋጅ ነው” አለች። “ሠረተኞች አወጁን ታገሉት፣ በአዋጁ ሥር አትደራጁ” ብላ ጥሪ አስተላለፈች። ዛሬ ላይ ሆነን ስናያው፣ የባርነት አዋጅ የተባለው የወታደረዊው መንግሥት የሠራተኛ ሕግ፣ በአንፃራዊ መልኩ ከንጉሡ ድንጋጌ 49/54ም ሆነ ከኢሕአዴግ አዋጅ 42/85 ወይም ከተሻሻለው 377/96 ለሠራተኛው የተሻለ ሕግ ነበር። ቀደምት ሥረዓት-አልበኞች፣ ለምሣሌ፣ ፕሩውዶን የፈረንሣይን ሕገ-መንግሥት፣ ሕገ-መንግሥት በመሆኑ ምክንያት ብቻ እንደተቃወመ፣ ኢሕአፓም የሀገሪቱን የኢንዱስትሪ ግንኙነት የሚቋጭ ሕግ፣ ሕግ በመሆኑ ብቻ ተቃወመች። ፀረ-ሕግና ፀረ-ሥርዓት መሆኗን በግላጭ አሳየች። ሠራተኛው በምስቅልቅል (anarchy) ውስጥ ሥርዓት እንዲፈልግ ጠራች።

ቀጥላም ታይቶና ተሰምቶ በማይታወቅ ሁኔታ፣ “የኢትዮጵያ ላብአደሮች አብዮታዊ ማኅበር (ኢላአማ) የተሰኘ የራሷን ሕቡዕ የሠራተኛ ማኅበር አቋቁማ፣ ሠራተኞች በድብቅ ‘በኢላአማ’ ሥር እንዲደራጁ ቀሰቀሰች። ሠራተኞች በማኅበሯ ተደራጅተው የዚያን ጊዜው የፖለቲካ ቀልዷ ለነበረው ለዝነኛው፣ “ጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግሥት” እንዲታገሉ ጠራች።

በሌላም በኩል፣ የትርምስ (anarchy) መስመሯን የተቃወሙና ሕጉ በሚፈቅደው መሠረት የሚደራጁ ሠራተኞችንና የማኅበራት መሪዎችን በማዋከብና በግድያ ጭምር ለማጥፋት ተንቀሳቀሰች። ከዚህ አንፃር ሊጠቀሱ ከሚገባቸው መካከል የመላው ኢትዮጵያ ሠራተኞች ማኅበር (መኢሠማ) ሊቀመንበር የነበሩትን አቶ ቴዎድሮስ በቀለን በማኅበሩ ጽ/ቤት ውስጥ ገደለች። ቀጥሎም የቴዎድሮስ ምክትል የነበረውና ከግድያው በኋላ ተክቶ ይሠራ የነበረው አቶ ተመስገን ማዴቦም የቴዎድሮስ እጣ ፋንታ ደረሰው። ማርቆስ ሐጐስ በተኩስ ልውውጥ ከስድሰት ባልደረቦቹ ጋር ለሞት ተደረገ። ከብርሃንና ሰላም ዳሮ ነጋሽ ከዘጠኝ ሠራተኞች ጋር የኢሕአፓ የማስመታት ሰለባ ሆነች።

እነ ኃይሉ ዑርጌሣ የሚሠሩት ለዚህ ቡድን ነው። የሚደራጁት ከነዚህ ጋር ነው። የሜይ-ዴይን መታሰቢያ በዓል የሚያከብሩት፣ በዚህ ዓይነት የኢትዮጵያን ሠራተኞች ብሔራዊ ጽ/ቤት ደም ካስለመዱና የመሪዎቻቸውን ሕይወት ከቀጠፉት ጋር ነው።

እነዚህን ከመሳሰሉ በተናጠል ከመምታትና ከማስመታት፣ ከመግደልና ከማስገደል ባሻገርም፣ ኢሕአፓ ሠራተኛው በጅምላ እንዲመታ ኢሰበአዊ ድርጊት ፈጽማለች።ሚያዚያ 23፣ 1968 ዓ.ም. ሜይ-ዴይ በሚከበርበት ዕለት በአብዮት አደባባይ ሠራተኞችን የማስመታትና ከሠራተኞች ሞት ስለደርግ ጨካኝነት ማስረጃ

ለመፈልቀቅ (to extract evidence from the death of workers) የፈጸመችው መሠሪ ተግባር ለዚህ ጉልህ ማስረጃ ነው። ኢህአፓ አስቀድማ የወጣት ክንፍ ድርጅቷ አባሎቹን አነሳስቶ ከሠራተኛው ጋር በዓሉን እንዲያከብር ስታዝ፣ ማንም በማይበግረው የታጠቀ ኃይል ትታጀባላችሁ፣ ከለላና መከታ ይሰጣችኋል ብለ አበረታታች። በምሥጢር ደግሞ ታጣቂዎቿ ተቀላቅለው ግጭት እንዲፈጥሩ አዘጋጀች። በዕለቱም ሠራተኛው ከየአቅጣጫው በሰልፍ ወደ አደባባዩ ሲመጣ ተደባልቀው እንዲገቡ ካደረገች በኋላ፣ የፀጥታ ኃይሎችን በመተንኮስ ሠራተኛው ሕንፃዎች ላይ ለተጠመዱ መትረየሶች የእሳትራት እንዲሆኑ አደረገች። በዚያ ኢሰብአዊ ድርጊት የ23 ሠራተኞች ሕይወት አለፈ። ብዙዎች ቆሰሉ። ብዙዎችም ታፈሱ። ድርጊቱ በጊዜው ታቀነቅነው ለነበረው "ፋሺዝም በኢትዮጵያ ለመንገሱ" ማስረጃ ለማግኘት ነበር። ኢሕአፓ በግልጽ እንዲያውም በኩራት የሠራተኛውን ዕልቂት "ጓዶችና ምልዓተ-ሕዝቡ ከፋሽሰቶች ጋር ተፋለሙ" ብላ ተሳለቀች። በዚህ ዓይነት ለሥልጣን በተደረገ ተጋድሎ፣ ሠራተኞች ለሞት ተዳረጉ። ደምና እንባ ተራጭተው የኢሕአፓ የሥልጣን ጥም ሰለባና ጭዳ ሆኑ።

ለነ ኃይሉ ዑርጌሣ የሜይ-ዴይን መታሰቢያ በዓል የሚያስታውሳቸውና የሚያዘጋጅላችው በሠራተኛው ላይ ይኸ ዓይነት የጅምላ ግድያ በሜይ-ዴይ ዕለት እንዲፈፀም ያደረገ ቡድን ነው። እነርሱም የኢትዮጵያ ሠራተኞች "ልዩ እረኞችና ወር ተረኞች" ሆነው በዓሉን የሚያከብሩት፣ የፓል-ቶካቸውን ቋሚነትን የሚወስኑትና ድርጅት ለመፍጠር የሚንደፋደፉት ከዚህ ቡድን፤ ለዚህ ቡድን ነው።

እነዚህን ከዚህ በላይ በጥቅሉ የጠቀስኳቸውን፣ በ60ዎቹ ሁለተኛ አጋማሽ፣ በኢትዩጵያ ሠራተኞች ላይ የተፈፀሙትን ወንጀሎች ከታሪክ የማትማረው ኢሕአፓ ከሶስት አሥርተ-ዓመታት በኋለም ደግማለች። ለአብነትም ያህል፣

የኢትዮጵያ ሠራተኞች አንደገና ሲደራጁ ኢሕአፓ በሠራተኛው እንቅስቃሴ ውስጥ አንድ አማሽ ሠርጐ-ገብ አሰርጋ በማስገባት ችግር ለመፍጠር ጥረት አድርጋለች። ሁለተኛ፣ ከባሕር-ዳር ጨርቃጨርቅ ሠራተኛ ማኅበር፣ ለጨርቃጨርቅ፣ ቆዳና ልብስ ስፌት ፌዴሬሽን ተልኰ፣ ለኰንፌዴሬሽን ጽ/ቤት በቀረበ መረጃ ፣ ከጋይም ሞት ጋር በተያያዘ፣ ሁለት ንፁሓን ሠራተኞች በባሕር-ዳርና በዳንግላ መካከል በምትገኝ ትንሽ ከተማ አካባቢ ተገለውና በቀበሮ ጉድጓድ ተጥለው እንደተገኙ ሪፖርት በጽ/ቤታችን መኖሩ ሳይገለጽ መታለፍ የሌለበት ጉዳይ ነው። ሦስተኛ፣ ፈጽሞ ባልነበረችበትና ባልዋለችበት ከአገር አወጣጣችን፣ እራሷ ያካሄደችው ኦፕሬሽን በማስመሰል፣ "ዓርብ የተጀመረ ኦፕሬሽን ቅዳሜ ተጠናቀቀ" በሚል ርዕስ በአንድ በአገር ቤት በሚታተም ጋዜጣ አስወጥታለች። ይኸንኑን አስመልክቶ ናይሮቢ ሳለሁ አቶ መርሻ ዮሴፍን አነጋገሬ፣ ይህንን የምታወጡት እናንተ ናችሁ። ያልተደረገውን እንደተደረገ አስመስላችሁ ፍጹም ውሸት እንዲዘገብ ማድረጋችሁ በሠራተኛው እንቅስቃሴ ላይ አፍራሽ እንድምታ ስለሚኖረው፣ አስተባብሉ ብዬ ጠይቄአለሁ። በወቅቱም አቶ መርሻ "እኛ አናውቀውም። ይኸንን የሚያወጣው ተስፋዬ ታደሠ ነው። በጋይም መገደል ድርሻ ስላለው ከመዋቅር አስወጥተነዋል፣ እኛን አይወክልም፣ ይመታም ብለናል" በማለት ክደዋል። ይኸንኑ አብረውኝ ስደት ለወጡ ባልደረቦቼ ነግሬ፣ በጉዳዩ ላይ ከተነጋገርንበት በኋላ ለተስፋዬ ተደውሎ ዘገባውን እንዲያስተባብል አስጠይቄአለሁ። ይህ የምት ፍንጭ (clue) ከላይ በተራ ቁጥር ሁላት ከጠቀስኩት ዘገባ ጋር ሲመሳከር፣ ብዙ ምት የደረሰበት ሠራተኛ አሁንም እየተመታ መሆኑን ከጥርጣሬ በላይ ይመሰክራል። በዚች ግፍ በበዛባት ሀገራችን ፍትሕ ይበየን እንደሆነ፣ ሁሉም ብርሃን ያዩ ይሆናል። አራተኛ አልፎ ተርፎም፣ ቱባዎቹ ኢሕአፓዎች ሳይቀሩ፣ በአውሮፓና በአሜሪካ "የወያኔን መንጋጋ ፈልቅቀን፣ በእስኳድ አጅበን አስወጥተናቸው፤ በፓርቲው ላይ አሉባልታ ያስወራሉ በማለት ፈጽሞ ያላደረጉትን ፍፁም ውሸት ነዝተዋል። አወጣጣችንን በተመለከተ ከአዲስ አበባ እስከ ሞያሌ ከአንዴም ሁለቴ ተመላልሰው አጅግ አስቸጋሪ ጉዞአችንን ያቀናጁት በሕይወት ስላሉ ሁኔታው ሲፈቅድላቸው ምሥክርነታቸውን እንደሚሰጡ አምናለሁ። አምስተኛ ለስደት ከተዳረግንበት ጊዜ ጀምሮም፣ ወረቀት ሲንኰሻኰሽ በርግገው የሠራተኛውን እንቅስቃሴ ጥለው የፈረጠጡትን፤ ከርታታ አባሎቿን፤ አልባሌ ጋዜጦቿንና አንዳንድ የግል ጋዜጠኝነት ስም የተሸከሙ ነውረኞችንና ጋዜጦቻቸውን፤ ተጠቅማ የስም ማጥፋት ዘመቻ በማካሄድ በውጭ በተደረጉና ሊደረጉ በሚችሉ ጥረቶች ላይ እንቅፋት ሆናለች። ሰባተኛ በአሜሪካን በሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ተዋጥቶልን፣አብረውኝ ለተሰደዱ የሠራተኛ ማኅበራት መሪዎች ናይሮቢ ከተላከው $1300 የአሜሪካን ዶላር ወደ አንድ ሺህ የሚጠጋ ቀምታለች። ስምንተኛ "ገንዘባችንን በሉት" ብሎ የተናገረውን አንድ ስደተኛ የማኅበር መሪ የመርሻ አጃቢዎች ለ15 ቀናት በመጠለያ ውስጥ አግተውታል። ዘጠነኛ ከላይ የጠቀስኳቸውን ድርጊቶች ቡድናቸው እንዲያርም፣ ከሚያካሄደው ጥቃትና የስም ማጉደፍ ዘመቻም እንዲቆጠብ፣ አቶ መርሻ አምስተርዳም በመጣ ወቅት፣ ለሁለተኛ ጊዜ አነጋግሬው ነበር። ሆኖም አንዳችም የተወሰደ እርምጃም ሆነ የተደረገ እርምት አልነበረም። አሥረኛ እጅግ አስነዋሪ በሆነ ሁኔታ የከፈቱብንን የጥቃት ዘመቻ በዓለም አቀፍ የትግል አንድነት መንፈስ አብረውን ወደ ቆሙት አጋሮቻችንም በማራዘም በውጭ የተከፈተ ጽ/ቤት እንዲዘጋ ምክንያት ሆነዋል። በአጭሩ፣ ኢሕአፓ መመልመል ስትፈልግ ሻንጣ ተሸክማ፣ ግጥም ገጥማ፣ አገልግል ጭና ስትከተል፤ ለስደት ላበቃን ዓላማ ፀንተን መቆማችን ስትረዳ ደግሞ ከኢሕአድግ በአቅም እንጂ በባሕሪዩ በማይለይ፣ ግን በአረመኔነቱ (barbarity) በሚልቅ ሁኔታ ስታጠቀን ቆይታለች።

ይህንኑ ሁሉ ፈርጀ-ብዙ ጥቃት በወቅቱ ለኢትዮጵያ ሠራተኞች ሳናሳውቅ የቆየነው በሁለት ምክንቶች ነበር። አንደኛው ምክንያት ሙታንንና ከነርሱም ጋር የተሰለፉትን፣ ተናግረናቸው እንዳናኖራቸው፣ አፍ ተካፍተን

ከትብያ እንዳንቀሰቅሳቸው በማሰብ ነበር። ሁለተኛው ምክንያት በሠራተኛው እንቅስቃሴ ውስጥ የታዩ ዝንፈቶችንና ውዝግቦችን አደባባይ በማውጣት የሠራተኛው የውስጥ ባላንጣዎችም ሆኑ አፋኞች እንዳይጠቀሙበት በማሰብ ነበር። በነዚህ ምክንያቶች የውስጥ ችግሮችን በውስጥ ይዞ መቆየቱ በአንድ ጐኑ የጠቀመ ሲሆን፣ በሌላ ጐኑ ጉዳት አስከትሏል። የሠራተኛው እንቅስቃሴ ባላንጣዎች (adversaries) እንዳይጠቀሙበት መታገሱ ጠቃሚ ነበር። መረጃዎችን ከጉዳዩ ባለቤት ሸፍኖ አሁን እየተገፋ ባለው ሁኔታ በሠራተኛው ስም ለሚነግዱት ዕድል መስጠቱ ደግሞ ጐጂም ስሕተትም ነበር።

አሁን ግን ቀድሞውኑ ሠርጐ- ገብ በነበረ አንድ ግለሰብ አጋፋሪነት፣ ጥቂት ለኢትዮጵያ ሠራተኞች የገቡትን ቃል ኪዳን ያላሉና ኃላፊነታቸውን የበሉ መንፈሰ ወላዋዮች በውስጥ ችግር ከመፍጠርና መሰናክል ከመሆን አልፈው፤ ተለጣፊ ድርጅት እስከማቋቋም እየዘለቁ በመሆኑ፤ ሲካሄድ የቆየውንና እየተካሄደ ያለውን በጐም ሆነ ክፉ ሠራተኛው ለቅሞና አበጥሮ ማወቁ መብቱ ከመሆኑም በላይ ከየአቅጣጨው ያለበትን አደጋ ከወዲሁ ተገንዝቦ፣ ወደፊት ድቅድቅ ጨለማው ሲገፍ፣ ማኅበሩን መልሶ ለማቆምና መብትና ጥቅሙን ለማስከበር ሊረዳው ስለሚችል፣ የዚህን መረጃ ማሰራጨት አስፈላጊነት አምኜበታለሁ። ስለሆነም፡-

- በመደራጀት ላይ የሚገኘው "የኢትዮጵያ ሠራተኞች ድምፅ፣ ወይም የኢትዮጵያ ሠረተኞች ጥምረት፣ ወይም የኢትዮጵያ ሠራተኞች የዲሞክራሲና የሰላም መድረክ" የኢሕአፓ ተለጣፊ ሥረዓተ-የለሽ ማኅበርተኛ ቡድን (EPRP anarcho-syndicalist group) ለመሆኑ ከጥርጣሬ በላይ (beyond doubt) የተረጋገጠ ነው። ለዚሁም፤ ሀ/የእንቅስቃሴው መድረክ ጠንሳሽ የአሲምባ ቡድን መሆኑ፤ ለ/ቀንደኛ ተዋናዮቹ  የኢዴኃኅ ድጋፍ ኰሚቴዎች ኃለፊ እና ቀድሞውኑ በሠራተኛው እንቅስቃሴ ውስጥ የኢሕአፓ ሠርጐ-ገብ የነበረ ግለሰብ መሆናቸው፤ ሐ/ ግለሰቦቹ ለኢትዮጵያ ሠራተኞች ከገቡት "ለነፃ ሠራተኛ ማኅበር፣ ራሱን ችሎ ለቆመ ሠራተኛ ማኅበር፣ ለዲሞክራሲያዊ ሠራተኛ ማኅበር" ከመቆም ቃለ-ማሃላ አፈንግጠው፤ የሠራተኛውን ቋንቋ እየናገሩ፣ በሥረዓተ-አልበኞች ቃላትና ሐረጐች ደንባቸውን እያረቀቁ መሆናቸው በቂ ማስረጃ ነው። ለምሣሌም ያህል፡ እየተወያዩበት ያለ ደንባቸው፣ "መድረኩ…ለፖለቲካ ተግባር እንደሠረገላ ሆኖ ያገለግላል (The Forum… will serve as vehicle for political activity)፤ የትብብርን አስፈላጊነት በመገንዘብ (cognizant of the significance of cooperation…)፤ ከሌሎች ሲቪክ እህት ድርጅቶች ጋር ለመሥራት (…work with other sisterly civic…organizations)" የሚሉ አንቀጾች ይገኙበታል። "ለፖለቲካ ተግባር እንደሠረገላ ሆኖ ያገለግላል" የሚለው ሐረግ  የተልዕኰአቸውን ምንነት ያለተጨማሪ ማብራሪያ የሚገልጽ ሲሆን፣ በትብብር አፈላጊነት ላይ የተቀረፀውም ቢሆን፤ ከማንና ለማን እየሠሩ እንዳሉ የአደባባይ ምሥጢር ስለሆነ የሚያሻማ አይደለም። ከሌሎች የሲቪል ሕብረተሰብ ጋር የመሥራቱ ጉዳይም ቢሆን፣ አናርኪዝም በመርሆዎቹ የቀረፀው ሕብረተሰብም ሆነ ሀገር በምድር ላይ ሰላልታየ፤እነዚህ ሰዎች ኢ-ሲቪል ስንጥቃት (uncivil interstices) ይፈጥሩ እንደሆነ እንጂ፣ የቆሙበት ሥፍራና ባሕሪይ ከሲቪል ሕብረተሰብ ድርጅቶች ጋር የሚያሰልፋቸው አይሆንም። (የዚህ እንቅስቃሴ ቀንደኛ ተዋናይ የሆኑ ግለሰቦች በሠራተኛው እንቅስቃሴ ውስጥ የነበራቸውን ሚና፣ እንዴት በሠራተኛው እንቅስቃሴ ውስጥ እንደ ተቀላቀሉ፣ እንዴት እንደወጡና ከወጡም በኋላ የተከተሉትን መስመር በተመለከተ በተከታይ መጣጥፎች በዝርዝር አወጠዋለሁ። )

- ከዚሁ ጋር በተያያዘ፣ ባለማወቅ በዚህ በታሪክ በሚያስወቅስና የትም በማያደርስ የኢሕአፓ እንቅስቃሴ ውስጥ የገባችሁ ወንድሞች፣ አቋማችሁን እንድትመረምሩ ጥሪዮን አቀርባለሁ። ይኸን ማድረግ የማትችሉ ከሆነ ግን፣ ከራሳችሁ በስተቀር የምትወክሉት የሌለ መሆኑን አውቃችሁ፣ በግላችሁ ባላችሁ ነፃነት በገባችሁበት መዳከር የምትችሉ መሆኑን፤ ግና የምትደርጉትን ከ32 በማናንሰው ተሰደጅ የማኅበራት መሪዎች ሰም፣ ወይም በሠራተኛ ማኅበራት ስም፣ ወይም በኢትዮጵያ ሠራተኞች ስም ማድረግ ፈጽሞ የማትችሉ መሆኑን፣ ነጮቹ 'በስማችን አይደለም (Not in our name) በሚሉት አጭርና ግልጽ ቋንቋ ላስጠነቅቃችሁ እወዳለሁ። የምታደርጉትን በተሰዳጅ የማኅበራት ስም አታድርጉ አላለሁ። የምታደርጉትን በማኅበራት ስም አታድርጉ እላለሁ። የምታደርጉትን በኢትዮጵያ ሠራተኞች ስም አታድርጉት እላለሁ።

- በዚህ አስነዋሪ እንቅስቃሴ ውስጥ የሌላችሁ ተሰዳጅ የሠራተኛ ማኅበራት መሪዎች፡ ፍቃዱ ጠንክር (አውስጥራሊያ)፣ ሚካኤል ቦካ (አውስትራሊያ)፣ ታደለ መብራቱ (ስዊዘርላንድ)፣ ሞገስ ኃ/ማሪም (ጀርመን)፣ እቴነሽ ሽታዬ (ጀርመን)፣ አባይነህ ማሞ (ጀርመን)፣ ዮሓንስ አክሊሉ (ጀርመን)፣ አሊ ሰይድ (ሆላነድ)፣ ተሾመ ባሳዝነው (ሆላነድ)፣ ቢራሳ አያና (ሆላንድ)፣ ኃይማኖት በላይ (ሆላንድ)፣ ጽጌ መርጊያ (አየርላንድ)፣ ማሞ ባሳዝን (ኖርዌ)፣ በቀለ መንግሥቱ (ካናዳ)፣ አብረሃም ተወልደ (ካናዳ)፣ ሰለሞን ወንድአየሁ (ዩኤስኤ)፣ ገነት ጥለሁን (ዩኤስኤ)፣ ተድላ ፋንታዬ (ዩኤስኤ) ተስፉ ተሾመ (ዩኤስኤ)፣ ጌታቸው አረጋ ( ዩእስኤ)፣ ጌታቸው መንግሥቱ (ዩኤስኤ)፣ ምትኩ ብርሃኑ (ዩኤስኤ)፣ ክንፈ ጋሻው (ዩኤስኤ) ሁላችሁም እየተካሄደ ባለው ዓይን ያወጣ ሤራ ላይ ያላችሁን አስተያየት፣ መደረግ አለበት ብላችሁ የምታምኑትንና ሙሉ አድራሻችሁን በኢ-ሜይል ibidunet@yahoo.com  እንድትልኩልኝ እጠይቃለሁ።

- ከሁሉም በላይ መብትና ጥቅማችሁን ማስከበሩ ቀርቶ ሕልውናችሁ አደጋ ላይ የወደቀው የኢትዮጵያ ሠራተኞች፣ ማኅበራትና ሐቀኛ የማኅበራት መሪዎች፤ ከዚህ በላይ ያሠፈርኳቸውን ታሪካዊና ወቅታዊ መረጃዎች (information) አውቃችሁ፣ በስማችሁ እየነገዱ ያሉትን ተረኛ ከሃዲዎች እንድትወግዙ እጠይቃለሁ።

የሠራተኛ ማኅበራት የውሃ ቦይ አይደሉም!!!
ትግሉ ይቀጥላል።